# Car Seats COLORADO

# መሠረታዊ መመሪያ

## የመኪና ላይ ወንበር፣ ለልጆች የወንበር ከፍ ማድረጊያ፣ እና የወንበር ላይ ቀበቶ ሕጎች እና መመሪያዎች

**አማርኛ**
**AMHARIC**

### ❖ የወንበር ላይ ቀበቶን ለልጅዎ ይሰሩ አልያ ይቀጣሉ

የትራፊክ ተቆጣጣሪዎች (ደንብ አስከባሪዎች) በተሽከርካሪ ውስጥ ወንበር ላይ ቀበቶ ያልታሰረለት ወይም አግባብ ባልሆነ መንገድ የታሰረለት ህጻን ወይም ልጅ ካዩ አሽከርካሪውን ማስቆም ይችላሉ። ዝቅተኛው ቅጣትም በአንድ ጊዜ ጥፋት/ሕግ ጥሰት $82 ነው።

### ❖ የኋለኛው ወንበር ይመረጣል

ከ13 ዓመት በታች የሆኑ ሁሉም ልጆች ኋላ ወንበር ላይ መቀመጥ እና ሁልጊዜም በተገቢው መንገድ፥ በተለይም መሃከለኛው ወንበር ላይ፣ ሊታሰሩ (ቀበቶ ሊደረግላቸው) ይገባል።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **የልጆች የመኪና ላይ ወንበር** | **ወደኋላ-የዞሩ የመኪና ውስጥ ወንበሮች/መቀመጫዎች** | **ወደፊት-የዞሩ የመኪና ውስጥ ወንበሮች/መቀመጫዎች** | **ከፍ ያለ መደገፊያ ያላቸው ወይም የሌላቸው የልጆች ወንበሮች/መቀመጫዎች** | **በጭን እና በትከሻ ላይ የሚታሰሩ የወንበር ቀበቶዎች** |
| **እድሜ** | **አዲስ ከተወለደ ጨቅላ እስከ 3 ዓመት**<br>(እስከተቻለ ድረስ ወደኋላ አዙሮ ማስቀመጥ) | **ከ2 እስከ 5 ዓመት** | **ከ4 እስከ 12 ዓመት**<br>(ወይም ለመደበኛ የወንበር ቀበቶ ብቁ እስከሚሆን/እስከምትሆን ድረስ) | **ከ8 ዓመት በላይ**<br>(ለአንዳንድ ልጆች፣ እስከ 12 ዓመት ድረስ አይሆንም) |
| **ክብደት/ቁመት** | የልጆች መኪና ውስጥ ወንበሮችን ፋብሪካው ከፍተኛ ክብደት ወይም ቁመት ብሎ በሰጠው መሠረት ይጠቀሙ። | | | መደበኛ የወንበር ቀበቶ ለመጠቀም ብቁ በሚሆን/በምትሆን ጊዜ። |

**ከዚህ በላይ የተሰጡት መመሪያዎች በNHTSA ምክሮች ላይ የተመረኮዙ ናቸው። የበለጠ ለመረዳት CarSeatsColorado.com ን ይጎብኙ።**

### ❖ ጠቃሚ ማስታዎሻዎች፡-

1. የልጅዎ የመኪና ላይ ወንበር ጊዜው ያላለፈበት መሆኑን ያረጋግጡ። በጊዜ ብዛት ወንበሩ የተሠራባቸውን ጥሬ እቃቆች ፀሐይ/ሙቀት እና ቅዝቃዜ ያዳከማቸዋል።
2. የልጅዎ የመኪና ላይ ወንበር እንዲሰበሰብ አምራቹ ጠይቆ ከሆነ ኢንተርኔት ላይ/ኦንላይን ያረጋግጡ።
3. ግጭት የደረሰባቸው የልጆች የመኪና ላይ ወንበር ጥሩ ቢመስሉ እንኳን አስተማማኝ አይሆኑም።

COLORADO
Department of Transportation